# ወይ ምስር እንዲህ ሆነክን?

*ከሥርጉተ ሥላሴ*

*ህዳር 2003 ዓ.ም*

ከሸፍታ ጋር መሸፈት አሰኝቶኛል ብሎ ምስርም አደመ አሉ። በዚህ መላ ቅጡ በጠፋበት ዘመን የማይሰማ ጉድ እኮ የለም። ምስር ለኪሎ 40.00 አርባ ብር፣ አንድ ብርት ድስት የማይሞላ የምስር ዋጋ ነው ኢትዮጵያ ላይ አርባ ብር የሚሸጠው።

የአንድ ኪሎ ምስር ዋጋ 40.00 ብር ሲሆን የአንድ ዶሮ ዋጋማ ምን ሊሆን ይችል ይሆን። ለመሆኑ አንድ ኪሎ ምስር ወጥ ሲሰራ ዘይት ሽንኩርት ውሃው በርበሬው ጨው ቅመም ከሰሉ ጉልበቱ እና ማባያው እንጀራ ሲጨመር ቤት ሆቴል ቤት ሆኖ ቁጭ አለ ማለት ነው።

ይህ እንግዲህ ቢበዛ  ሁለት ሰው ይሆናል የሚያጠግበው። ወይ ጉድ ቃሉን መግለጹ እራሱ ሊያሰቀጣኝ ይገባል .. " <u>ጥጋብ</u>" አልኩት ይገርማል ... ጽድቁስ ቀርቶ በወጉ በኮነነኝ ዓይነት ሆኖ ከአለግባብ ቃሉን ተጠቀምኩበት። በ እውነት ከምር ልቀጣ ይገባል።

መልካሙ ዘምንማ አመለጠ። አሁን በአራዊቱ ኮረኮንች ዘመን ህዝብ ባልበላ አንጀቱ ተቀጠቀጠ፤ ከተዘቀዘቀቀ ተስፋ ጋር ተጋብቶ ወገናችን ታመሰ - ተነገረገበ። አንድ ኪሎ ምስር 40.00 ብር እኔ እኮ እራሱ ማመን ነው ያቃተኝ።

እንዲያው ይህን ገዝቶ መብላት የሚችለው ወገን እጣ ፋንታ ሲሆንነ። ጭራሽ የማይችለው በሚሊዮን የሚቆጠረው ወገንስ እሰኪ ትንሽ እራቅ ብለን እንጓዝ እና ሊለምን ያፈረው ወገን ምን ያህል ሚሊዎን ሊሆን እንደሚችል እንገምተው በጣም ጉድ እኮ ነው

ወያኔ እንዲህ እረግረግ ላይ ህዝቡን ጨምሮ ነው የአምስት ዓመት ፕላን እያላ የሚያላግጠው፣ የሚደልቀው። ሕዝባችን የቀን ጨለማ ውጦት እሱ ሰለ ኮንሰትራክሽን ይፎክራል። ድንቄም ...

መጀመሪያ ህዝቡ የጉሮሮ ማርጠቢያ ለጥጋብ ሳይሆን ወስፋቱን ለሚያሰርፈበት ብጣቂ ነገር ይብቃ፤ ለራበው ህዝብ የነፍስ ማሳደሪያ ቁራሽ ብቻ ...  ነው የሚያስፈልገው። እሱን ለደላቸው ለወያኔ ሹማምንት ቤተሰቦች ...

እጅግ እኮ የሚነመዝዝ ጉድ እኮ ነው። እንዲያው ምን እና ምንኑ አድርጎ ይሆን ያ መከረኛ ህዝብ መሽቶ የሚነጋለት። እንዲህ እንደ
አነባ - እንደአዘነ እርር ኩምትር ጭብጥ እንዳለ ሊያልፍ ....

ከቶ ... ያልፋልን ሲጠብቅ እሱም ለራሬ ሳይበቃ እህል እንደ አመረው እንደ ናፈቀው በቃ እልፍ ... ሊል ... ወይ የቅጣቱ ብዛት እርሃቡ፣ እርዛቱ፣ በሽታው፣ ግፉ፣ ሌላም አለ እኮ ... በደሉ መጠነ ሰፊ ነው። በራህብ ላይ በተስፋ ማጥት ላይ ደግሞ እስራትም ግርፊያም ሞትም አለ ...

መቼ እና መቼ ተጋብተው ይሆን የወያኔን እልፈት የ ሚያውጁት? መቼ ይሆን ይህ ጠቀራማ ዘመን ከነድሪቶው የሚሰናበተው፣ መቼ ይሆን ህዝብ ከስጋት ኑሮ ተላቆ በሀገሩ አንጡራ ሀብት ብቸኛ ተጠቃሚ ሆኖ ቢያነስ ለጉሮሮው፣ ለመጠለያው፣ ለቁራሽ በቅቶ የሚታዬው ...

ወያኔ እኮ የመጣበትን ተልእኮ እያፈጸመ ነው። ሁሉንም ማጥፋት። ብርሃን ገድሎ ጨለማን መነገስ፣ የበቀል ፕሮጀክቱ ነበር ተሳካለት። እኛስ ምን እያደረግን ይሆን ... እንዲህ እንደ አሾፈብን እንደ ቀለደብን ከቧልቱ ጋር የጎሪጥ እየተያን መኖር ወይስ ,፣?

የፈጠረን አምላክ በቃችሁ ይበለን አሜን።